# ነገረ ድኅነት



በሰንበት ት/ቤቶች ለሚማሩ የከፍተኛ ትምህርት
ተቋማት ተማሪዎች መማሪያ የተዘጋጀ

# ነገረ ድኅነት

## በሰንበት ት/ቤቶች ለሚማሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች መማሪያ የተዘጋጀ

አዘጋጅ፡- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል
1993 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ትቤቶች ማደራጃ መምሪያ
የማኅበረ ቅዱሳን ቤተ መጻሕፍት
MAHIBERE KIDUSAN LIBRARY

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ


መቅድም ........................................ 3

1. ነገረ ድኅነት ........................................ 4
2. የአዳም አወዳደቅ ........................................ 4
3. ለአዳም መሳሳት ተጠያቂው ማን ነው? ........................ 7
4. የአዳም ውድቀት ስንል ምን ማለታችን ነው? ................ 9
5. ለአዳም የሚያስፈልገው ማን ነው? ............................ 11
6. እግዚአብሔር ለምን ሰው ሆነ? ................................ 14
7. እግዚአብሔር ሰውን እንዴት አዳነው? ........................ 15
8. እግዚአብሔር ሰው ሆነ ስንል እንዴት ነው? ................ 17
9. ነገረ ማርያም በነገረ ድኅነት ................................ 25
10. በነገረ ድኅነት ውስጥ የሰው ልጅ ድርሻ ምንድን ነው?. 29





ቤተ መጻሕፍት ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን
MAHIBERE KIDUSAN LIBRARY

# መቅድም

የመዳን ትምህርት የቤተክርስቲያን ትምህርት ማዕከል ነው። የመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የሌሎች መጻሕፍት ዋና ዓላማ ሰው የሚድንበትን መንገድ ማሳየት ነው። መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስም የሞተው የሰውን ልጅ ለማዳን ነው።

የመናፍቃን የክህደት መነሻ ትክክለኛውን የመዳን መንገድ በመሳትና በማሳት በመሆኑ ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ አበው ምሥጢረ ሥጋዌን አምልተውና አስፍተው በማስተማርና በመጻፍ ነገረ ድኅነትን የትምህርታቸው መነሻና መድረሻ አድርገውታል።

ይህ ትምህርት የተዘጋጀው ለግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ሊረዳ በሚችል መንገድ የአበውን ትምህርት መሠረት በማድረግ ነው። የሚያስተምረው መምህር፦

- ❖ ምሥጢረ ሥጋዌንና ምሥጢረ ሥላሴን አስቀድሞ ቢማርና በሚገባ ቢያውቅ
- ❖ ሃይማኖተ አበውን ቢያነብና የአበውን ይትበሃልና ትርጉም ለቅሞ ቢይዝ
- ❖ የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክን ቢያነብና ማስታወሻ ቢይዝ ትምህርቱን በሚገባ ለማስተማር ይረዳዋል።

ከዚህም በተጨማሪ። ነገረ ድኅነት መሠረታዊውን የቤተክርስቲያን ትምህርት /አምስቱ አዕማደ ምሥጢር፣ ሰባቱን ምሥጢራት ቤተክርስቲያን፣ የቤተክርስቲያን ታሪክ/ ከተማሩ በኋላ ሊሰጥ የሚገባው መሆኑን ልንጠቁም እንወዳለን።

የማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል

# ነገረ ድኅነት

«ነገር» የሚለው ቃል በቤተክርስቲያን ትምህርት የአንድን ትምህርት መስክ መግለጫ ሆኖ ያገለግላል። ለምሳሌ« ነገረ ማርያም» ሲል ስለ እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለሰው ልጅ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተገለጠውን ሁሉ የምንማርበት ትምህርት ማለት ነው። በዚህ ይዘቱ/ LOGY / የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ይመስላል።

## ድኅነት

በቤተክርስቲያን ትምህርት ድኅነት ማለት ከኃጢአት ተፈውሶ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሽ መሆን ማለት ነው።

«ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ» ማቴ 1÷21 የነገረ ድኅነት ትምህርት ባንድ ወገን አባታችን አዳም ከወደቀበት የኃጢአት ማጥ ወጥቶ እንዴት ዳነ? በሌላው ወገን ደግሞ እኛ ልጆቹስ እንዴት እንድናለን? የሚሉትን ነጥቦች የምናይበት ትምህርት ነው።

የነገረ ድኅነት መነሻው የአዳም ውድቀት ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ኃጢአትን የሠራ፣ይድን ዘንድም ቃል ኪዳን የተገባለት የመጀመሪያው ሰው እርሱ ነውና። በመሆኑም ትምህርታችንን የምንጀምረው ከዚሁ ነው።

## የአዳም አወዳደቅ

እግዚአብሔር አምላክ አምስት ቀን ሙሉ ዓለምን በሥነ ፍጥረት እያስጌጠ ካዘጋጀ በኋላ በ6ኛው ቀን ታላቁን የሥነ ፍጥረት እንግዳ ሰውን ፈጠረ። የቤተክርስቲያናችን ሊቃውንት ስለዚህ ጉዳይ ሲያስረዱ «አንድ ደግ ሰው እንግዳ ሲጋብዝ አስቀድሞ ቤቱን፣መብል መጠጡን ሌላውንም ነገር እንዲያዘጋጅ እግዚአብሔር አስቀድሞ የሚተነፍሰውን አየር፣የሚጠጣውን ውኃ፣ የሚበላውን ምግብ፣የሚኖርባትን ገነት እንዲሁም ለአንክሮ ለተዘክሮ የሆኑትን ሁሉ ካዘጋጀ በኋላ አዳምን ፈጠረው።»

አዳም የተፈጠረው በነፃነት የዚህ ዓለም ገዥ ናዛዥ ሆኖ ሊኖር ነው። በእግዚአብሔር አርአያና መልክ የተፈጠረ ብቸኛ ፍጡር ነው።«ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፣እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።» ዘፍ 1÷26። እግዚአብሔር ለአዳም ያለውን ፍቅር በሥነ ፍጥረቱ፣አክብሮ አልቆ በአርአያው በምሳሌው በመፍጠሩ፣ከርሱ በታች በሰጠው የገዥነት ሥልጣን ታውቋል።

<u>ዕፀ በለስ ለምን ተፈጠረች?</u>

1. <u>አዳም ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር እንዲገለጥ ነው።</u>

አንዳንድ የዋሐን «ዕፀ በለስ ባትፈጠር ኖሮ አዳም ባልተሳሳተም ነበር።» እያሉ የሞኝ ቁጭት ይቆጫሉ።

## <u>ዕፀበለስ የተፈጠረችው:-</u>

እግዚአብሔር ለአዳም ያለው ፍቅር ከመፍጠር እስከ መግቦት ባለው ተገልጧል። የአዳምስ? የአዳም ፍቅር የሚታወቀው ደግሞ የፈጣሪውን ሕግና ትእዛዝ በማክበር ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው፣የሚጠብ ቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው» ዮሐ 14÷21 በማለት እንዳስተማረን። የእግዚአብሔር ወዳጅ ለመባል ሁለት ነገሮች ያስፈልጋሉ።

1. «ትዕዛዜ በርሱ ዘንድ ያለችው» የእግዚአብሔር ትእዛዝ ያለው

2. «የሚጠብ ቃትም» የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚጠብቅ

እግዚአብሔርም የአዳም ፍቅር ይታወቅ ዘንድ ትእዛዝ መስጠት፣አዳምም መጠበቅ ነበረበት። በመሆኑም ዕፀ በለስ የሕግ ዛፍ ሆና ተሰጠችው።«ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ፤ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» ዘፍ 2÷16። ይህን ትእዛዝ በማክበር አዳም ከክብሩ ሳይጐድልበት ከጸጋው ሳይቀነስበት ለሰባት ዓመታት መኖሩን ሊ ቋንት ያስተምሩናል። «ትእዛዙን የሚጠ ብቅ በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም ይኖርበታል» 1ዮሐ 3÷24

እንደተባለ አዳም በእግዚአብሔር ቤት እግዚአብሔርም በአዳም ልቡና ኖ ሩ፡

2. ፍጡርነቱ ይታወቅ ዘንድ ነው

ዲያብሎስ ፍጡርነቱን ረስቶ ፈጥሬያለሁ በማለቱ«ጥንቸል በሬን አክላለሁ» ብላ ፈንድታ እንደሞተችው እርሱም በትዕቢቱ ወደቀ:: ስለዚህም እግዚአብሔር ለአዳም ፍጡር መሆኑንና ፈጣሪ እንዳለው የምታሳውቅ ምልክት/የተገዥነት/ ሰጠው:: ትእዛዝ ሰጭ እንዳለው ትእዛዝ ተቀባይ በመሆኑ ታወቀ«ሁሉን ግዛ ቢባልም«ሁሉን ካስገዛለት ከእግዚአብሔር» በታች መሆኑ አድርግ አታድርግ በሚለው ሕግ ታወቀ::

3. ነፃ ፈቃዱ ይገለጥ ዘንድ

የአንድ ሰው ነፃ ፈቃዱ የሚታወቀው የመምረጥ መብት ሲኖረው ነው:: ያለበለዚያ ግን መመሪያ እንጂ ነፃ ፈቃድ አይሆንም:: እግዚአብሔርም ለአዳም «ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» ዘፍ 2÷17::

አዳም ሁለት ምርጫ ተሰጠው:: የሚበላቸው ሌሎች ዛፎችና የማይበላት ዕፀ በለስ:: ሌሎችን ዛፎች ቢበላ በሕይወት ይኖራል:: ዕፀ በለስን ቢበላ ግን ይሞታል:: እሳትና ውኃ ከፊቱ ቀርቦሊታል ወደ ወደደው እጁን መዘርጋት የአዳም ድርሻ ነው::

«ተመልከት፤ ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን፣ ሞትንና ክፉትን አኑሬአለሁ:: በሕይወትም እንድትኖር እንድትበዛም፣ አምላክህም እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባባት ምድር እንዲባርክህ፣ አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ ትእዛዙንና ሥርዓቱን ፍርዱንም ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ እኔ አዝዝሃለሁ:: ልብህ ግን ቢስት አንተም ባትሰማ፣ ብትታለልም ለሌሎችም አማልክት ብትሰግድ ብታመልካቸውም ፈጽማችሁ እንድትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኋለሁ::» /ዘዳ. 30÷15–18/:: በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ:: ...እርሱ ሕይወትህ

የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድደው፣ ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ። ዘዳ 30÷19–20።

በመሆኑም ዕፀ በለስ የተፈጠረችው በነዚህ ሦስት ምክንያቶች እንጂ አዳምን ለማሳሳት አይደለም። እግዚአብሔር አዳምን ይሳሳት ዘንድ አሳልፎ አልሰጠውም፤ አስተማረው መከረው እንጂ። የዕፀ በለስን የመፈጠሯን ምክንያት ባይነግረው ኖሮ አዳም ባለማወቅ ተሳሳተ ባልን ነበር።

አዳም ወዶ ፈቅዶ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ለትእዛዙም እንዲገዛ እግዚአብሔር መብት ይሰጠው ዘንድ ዕፀ በለስን ባይፈጥርለት ኖሮ ወዶ ፈቅዶ መርጦ መታዘዙን ማወቅ ባልቻልን ነበር።

ለምሳሌ አንድ አባት ልጆቹ ሥጋ ብቻ እንዲበሉለት ይፈልጋል። ጠንካራ ሆነው ማየት ስለሚፈልግ። ከሁለት ልጆቹ አንደኛው የሆድ በሽታ ስለያዘው ከሥጋ በቀር ሌላ ሊስማማው ባለመቻሉ ሥጋ ይባላ ነበር። ሁለተኛው ልጁ ግን የአትክልት ምግብ በጣም ይወድ ነበር። ሥጋ በመብላቱ አባቱ እንደሚደሰት ስላወቀ ሥጋ መብላት ጀመረ። ከሁለቱ አባቱን ያስደሰተው ማነው?

የመጀመሪያው ልጅ ሥጋ የሚበላው አማራጭ ስላጣ ነው። ሁለተኛው ልጅ ግን ከራሱ ፍላጐት የአባቱን፣ ከራሱ ፈቃድ የአባቱን መርጦ ፈቃዱን ትቶ ነው።

አዳምም እንዲሁ ነው። ዕፀ በለስ ባትኖር ኖሮ በፈቃዱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸሙ ባልታወቀ ነበር።

## ለአዳም መሳሳት ተጠያቂው ማነው?

1. የዕፀ በለስ መኖር ነውን?

ዕፀ በለስ በራስዋ ምንም ማድረግ የምትችል ፍጥረት አይደለችም። ወደ አዳም ተጉዛ ብላኝ አላለችም። ደግሞም ዕፀ በለስ በአዳም ላይ ሞት ያመጣችው መርዛማ በመሆንዋም አይደለም። ዕፀ በለስ ከላይ እንዳየነው የምልክት ዛፍ ናት። መታዘዝና አለመታዘዝን የምትገልጥ። አዳም ዕፀ በለስን ከበላህ ሞት ይመጣብሃል ካልበላህ በሕይወት ትኖራለህ ተብሏልና። ከሕይወትና ሞት እንዲመርጥ ምርጫ ተሰጥቶታል።

አዳም ሞትን መርጦ ዕፀ በለስን ቀጠፈ፡፡«ልሙት» ብሎ ወሰነ እንጂ ማንም አልወሰነበትም፡፡ እናም ዕፀ በለስ ተጠያቂ አይደለችም፡፡

2. ዲያብሎስ ነውን?

«አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፣ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ? . . . አንተም በልብህ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፡፡ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ድንኳኖች በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ. . . ከደመናዎችም ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፡፡ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ» ኢሳ 14÷12–14፡፡

«በሰማይም ሰልፍ ሆነ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉት፡፡ ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፡፡ አልቻላቸውም፡፡ ከዚያም ወዲያ በሰማይ ሥፍራ አልተገኘላቸውም፡፡ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱ የቀደመው እባብ ወደ ምድር ተጣለ፡፡» ራእይ 12÷7–10፡፡

ሰይጣን ራሱን ከክብር አዋርዶ ለሰይጣንነት የበቃ ነው፡፡ እንጨትና እንጨት ተፋጭቶ እሳት እንዲያመነጭ ሰይጣንም ትዕቢትንና ሐሰትን ከራሱ አፍልቆ ራሱን አጠፋ፡፡ዲያብሎስ እርሱ ያጣውን ክብር እኛም እንድናጣ ፈለገ፡፡ ስለሆነም ወደሔዋን መጣ፡፡ ክፉ ምክርንም መከራት፡፡ እግዚአብሔርን ውሸተኛ አድርጎ አቀረበላት፡፡ ሔዋንም ዕፀ በለስን ቀጠፈችና በላች፡፡

ታዲያ ዋናው ተጠያቂው ዲያብሎስ ነው? አይደለም፡፡ ዲያብሎስ ሔዋንን ክፉ ምክር መከራት፡፡ ዕፀ በለስን ብትበሉ አምላክ ትሆናላችሁ ብሎ፡፡ ሔዋን ዕፀ በለስን በተመለከተ ይህ ሁለተኛዋ ትምህርት ነው፡፡

የመጀመሪያው– ዕፀ በለሰን ብትበሉ ትሞታላችሁ –እግዚአብሔር
ሁለተኛው –ዕፀ በለስን ብትበሉ አምላክ ትሆናላችሁ –ሰይጣን

እግዚአብሔር የታመነ አምላክ መሆኑን የሰው ልጅ ፈትኖ ለማወቅ ችሏል፡፡ ለሰባት ዓመታት ሞትን ሳያይ በመኖሩ፡ ነገር ግን የዲያብሎስን ቃል ሰሙ እርሱ እግዚአብሔርን ውሸተኛ አድርጎ ሲያቀርብላቸው ተቀበሉት፡፡ አዳምና ሔዋን ወስነው

ፈቅድው ሕገ እግዚአብሔርን ጥሰው በዲያብሎስ ምክር ተመሩ፡ ዲያብሎስ እጃቸውን ይዞ አላስቆረጣቸውም:: ቁርጠም አላጐረሳቸውም:: መከራቸው እንጂ:: አመዛዝኖ መወሰን የአዳምና የሔዋን ድርሻ ነው:: ዲያብሎስ ምክንያተ ስህተት እንጂ ስህተት እንድናደርግ የማስገደድ መብት የለውም:: ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ«ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተ ቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል:: ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል::» ያዕ 4÷8:: እንዳለን ዲያብሎስን የመ ቃወም መብቱም ሥልጣኑም ነበራቸው:: እነርሱ ግን መብታቸውንና ሥልጣናቸውን አሳልፈው ሰጡት:: በመሆኑም ለአዳምና ለሔዋን መሳሳት ዲያብሎስ ተጠያቂ አይደለም:: ዋና ተጠያቂው ራሱ የሰው ልጅ ነው:: ለዚህም ነው ሔዋን በእባብ ያመካኘችውን ምክንያት እግዚአብሔር ያልተቀበላት::

<u>የአዳም ውድቀት ስንል ምን ማለታችን ነው</u>?

አዳም ወደቀ ስንል <u>ጸጋው ተገፈፈ ባሕርይው ጐሰቆለ</u> ማለታችን ነው::

1. **ጸጋው ተገፈፈ**

<u>ራቁቱን ሆነ</u>

ለአዳምና ለሔዋን የጸጋ ልብስ ነበራቸው:: ዕፀ በለስን በልተው ትእዛዙን ሲሽሩ ግን ራቁታቸውን ሆኑ« የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ እነርሱም ራቁታቸውን እንደሆኑ ዐወቁ» ዘፍ 3÷7:: ተፋፈ ሩ፡

<u>ኃይልን አጣ</u>

ፈ ቃደ ነፍስ በፈ ቃደ ሥጋ ላይ የነበራትን ኃይል አጣች:: የሰው ልጅ ለመብላት ባማረ፣ለዓይን በሚያስጐመጅ ለጥበብ መልካም መስሎ በሚታይ ነገር /ዘፍ 3÷6/ ተሸነፈ:: ሰው እንስሳትን ይመስል ለፈ ቃደ ሥጋው ድል ሆነ::

«ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ»:: መዝ 48÷12::

ለእንስሳት ስም ያወጣ የነበረው አዳም ስም ያወጣላቸውን እንስሳት ፈራ:: ከእግዚአብሔር ከአምላኩም ሸሸ:: የፍቅር

ድምፁን የሚያዳምጥበት መንፈሳዊ ኃይል አጣ፡፡ ኃጥእ ነውና ማንም ሳያሳድደው ሸሸ፡፡ ምሳሌ 28÷1« የኃጥእ ሰው ፍርሃት በላዩ ይመጣበታል፡፡» ምሳሌ 10÷24፡፡

እንግዳ ሆነ

የገነት ባለርስት የዚህ ዓለም ጌታ የነበረው የሰው ልጅ ርስቱን በማጣት እንግዳ ሆነ፡. ርስቱን የሚናፍቅ፡፡ ለዚህም ነበር በብሉይ ዘመን የነበ ሩ አበው እንግዶች ነን ያሉት፡፡

ፈርዖንም ያዕቆብን የዕድሜህ ዘመን ስንት ዓመት ነው? አለው ያዕቆብም ለፈርዖን የእንግድነቴ ዘመን መቶ ሠላሳ ዓመት ነው... አለው፡፡ ዘፍ 47÷8

«እኔ በምድር መጻተኛ ነኝና እንደ አባቶቼም እንግዳ ነኝ» መዝ 38÷13

2. ባሕርይው ጐሰቆለ

ሰላሙን አጣ

አዳም ሰላማዊ ሆኖ ነበር የተፈጠረው፡፡ ሕገ እግዚአብሔርን ሲሽር ግን ሰላሙን አጣ፡፡ ተጨነቀ፡፡ ደነገጠ፡፡ ተሸሸገ፡፡ ኃጥእ በሰላም መኖር አይቻለውምና መደበቂያ ፈለገ፡፡

ነጻነቱን አጣ

አዳም በነፃነት የሚኖር ነፃ ፍጡር ነበር፡፡ ሕይወትንም ሞትንም የመምረጥ መብት ነበረው፡፡ አሁን ግን ሞትን መርጦ በሞት ቀንበር ሥር ተያዘ፡፡ ሞት ሠለጠነበት፡፡ የሞት ባርያም ሆነ፡፡ «ከአዳም እስከ ሙሴ ሞት ነገሰ» ሮሜ 5÷14 እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ የአዳም ንጉሥነት ቀርቶ ባርያ ሆነ፡፡

ሕያውነትን አጣ

አዳም ሕያው ሆኖ ይኖር ዘንድ ቢፈጠርም ሞትን በገዛ እጁ በመጋበዙ ሟች ሆነ፡፡ እንደ እንስሳት መሞት መበስበስ ግድ ሆነበት፡፡ ፈ ቃዱን እንደ ፈጸመለት እንደ ዲያብሎስ በነፍስ ወደ ሲዖል መውረድን ተቀበለ፡፡ ይሠዋው የነበረው መሥዋዕትም ሟች፣ ሕይወትን የማያመጣ፣ ሞት የሚያሸንፈው የእንስሳት መሥዋዕት ሆነ፡፡

እግዚአብሔርን መምሰል አጣ

«እኔ ግን አማልክት ናችሁ አልሁ፣ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ:: ነገር ግን እንደሰው ትሞታላችሁ ከአለቆችም እንደ አንዱ ትወድ ቃ ችሁ:: መዝ 81÷6፣ ዮሐ 10÷34

ሰው አምላክ ዘበጸጋ ነበረ:: ነገር ግን እንደ ዲያብሎስ /ከአለቆች እንደአንዱ/ በመውደቁ እግዚአብሔርን የመምሰል ክብር አጣ::

ባለዕዳ ሆነ

አዳም በባሕርይው ነጻ ሰው ነበር:: አሁን ግን ዕዳን በገዛ እጁ አመጣ:: ሞትን ያህል ዕዳ ተሸከመ:: ደግሞም ዕዳውን መክፈል አልቻለም::

ገነትን አጣ

አዳም የነበረችውን ርስት አጥቶ ተባረረ:: ገነት ተዘጋችበት:: ስደተኛም ሆነ:: እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም:: ማቴ22÷32:: አዳምና ሔዋን ግን ሞትን ተሸከሙ:: ስለዚህም ከሕያዋን አምላክ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ግንኙነት ተቋረጠ::

ለአዳም የሚያስፈልገው ማነው? ነቢይ? መልአክ? ሌላ ፍጡር? አምላክ?

አዳም አባታችን ጸጋው ተገፏል፣ /ራቁቱን ሆኗል፣ ኃይሉን አጥቷል፣ እንግዳ ሆኗል/ ባሕርይው ጐስቁሏል/ሰላሙን አጥቷል፣ ነጻነቱን አጥቷል፣ ሕያውነትን አጥቷል፣ እግዚአብሔርን መምሰል አጥቷል፣ ባለዕዳ ሆኗል፣ ገነትን አጥቷል/ ታዲያ አዳምን ከዚህ ሁሉ ዕዳ አውጥቶ ምቶን አሸንፎ በሐዲስ ተፈጥሮ ሊፈጥረው የሚችል፣ ወደ ወጣበት ርስት የሚመልሰው ባለጸጋ የሚያደርገው ማነው?

ነቢይ ነውን?

ነቢያት ወደ ሕዝቡ ይላኩ የነበሩት ለሁለት ምክንያቶች ነበር:: የመጀመሪያው ለትምህርት ለተግሳጽ ነው:: ሙሴና ሳሙኤል ሕዝቡን ይመሩ ይመክሩ ይገስጹ እንደነበረው ማለት

ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ ከሚመጣው ቁጣ ይተርፍ ዘንድ መፃኢያቱን እየነገሩ ይመክራሉ ይገስፃሉ ያስጠነቅቃ ሉ:: ዳንኤልና ኤርምያስ ኢሳይያስና ሕዝቅኤል በሕዝበ እሥራኤል ላይ ከሚደርሰው ጉዳይ አንሥቶ በዓለም ላይ እስከሚፈጸመው ድረስ በትንቢት መጽሐፋቸው እንደገለጡት::

ነቢያት በየዘመናቱ ከደረሰውና ከሚደርሰው መከራ በምክራቸውና በትምህርታቸው በጸሎታቸውና በምልጃቸው ሕዝቡን ከመዓት ከቁጣ ከሞት አድነዋል:: መዝ 105÷23::

ይህ ሁሉ የነቢያት ተጋድሎ አዳምን ከሲኦል ወደገነት ሊመልሰው፣ከጥንተ አብሶ/ ከውርስ ኃጢአት/ አላቅቆ ነፃነት ሊሰጠው፣ ዕዳ ሞትን ሊከፍልለት አልቻለም::

እነርሱ ከአዳም ዕዳ ነፃ ስላልነበሩ ባለዕዳ ባለዕዳን ሊያድነው አልቻለም:: መዝ 63÷5:: በመሆኑም ለአዳም ከነቢያት የሚበልጥ አስፈለገው::

<u>መልአክ ነውን?</u>

መላእክት በሰው ና በእግዚአብሔር መካከል የሚላላኩ/ሉ ቃ 1÷18–19/ የሰዎችን ጸሎት የሚያሳርጉ/ራዕ 8÷1–5/፣ ስለ ሰዎች ኃጢአት የሚያማልዱ /ዘካ 1÷12–17/ ሰዎችን ከክፉት መከራ የሚያድኑ/ዘፍ 48÷16/፣ ከታናሽነት እስከ ዐዋቂነት የሚመግቡ /ዘፍ 48÷15/፣ በሰዎች ንስሐ መግባት የሚደሰቱ /ሉ ቃ 15÷7፣10/ናቸው:: በዚህ ሁሉ ተልእኰዋቸው የሰውን ልጅ በገነት ሳለ ከገነት ከተባረረም በኋላ ሲራዱት፣ ሲማልዱለት፣ መንገዱን ሲመሩት ኑረዋል::

ይህ ሁሉ ቢሆንም መላእክት አዳምን ከሲኦል ሊያወጡት፣ ገነትን ሊከፍቱለት፣ ሞትን ሊደመስሱለት አልቻሉም:: ምክንያቱም፤

1. ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ሲጣላ የእግዚአብሔር ከሆነ ጋር ሁሉ ተጣልቷል:: የእግዚአብሔር መላእክት ወደ አዳም ይመጡ ነበር እንጂ አዳም ወደነርሱ መሄድ አልቻለም::

2. በአዳም የሞት ፍርድ የፈረደው እግዚአብሔር በመሆኑ እግዚአብሔር የፈረደውን ፍርድ መላእክት ማንሣት አልቻሉም።
3. ከገነት አዳምን ያስወጣ በመልአኩ ሰይፍ ገነትን ያስጠበቀ፣ እግዚአብሔር በመሆኑ እግዚአብሔር ያስወጣውን አዳም መላእክት ሊመልሱት አልቻሉም።

በመሆኑም ለአዳም ከመላእክት የበለጠ ያሻው ነበር።

<u>መሥዋዕተ ኦሪት ነውን?</u>

ከዘመነ አበው እስከ ዘመነ ካህናት በተራሮችና በቤተመቅደስ መሥዋዕተ አበውና መሥዋዕተ ኦሪት ቀርበዋል። የበግና የላም የፍየል መሥዋዕት ግን አዳምን ሊያድነው አልቻለም።

1. የሚሠዋው መሥዋዕት የፍጡር በመሆኑ ፍጡርን ፍጡር ማዳን አይችልምና ሊያድነው አይችልም። ፍጡርን ፍጡር ሊያድነው ቢችል ኖሮ ፍጡርን ፍጡር ሊፈጥረው በቻለም ነበር። ከየት እንዳመጣው ፣ ምን እንደሰጠው ከሚያውቅ በቀር አዳምን ወዴት እንደሚወስደው ምንስ እንደሚመልስለት ሊያውቅ የሚችል አንዳች የለምና። በመሆኑም የፍጡር መሥዋዕት ፍጡርን ሊያድነው አልቻለም።/ዕብ. 10÷1–5/

2. የሚሠዋው መሥዋዕት ሞት የሚያሸንፈው በመሆኑ ሞትን ድል አድርጐ አዳምን ከሞት ባርነት ሊያወጣው አልቻለም። በጉም ሆነ ፍየሉ ሚች ሙቶ በስብሶ የሚቀር የሞትን መውጊያ፣ የመቃብርን መዝጊያ ማሸነፍ የማይችል በመሆኑ ባለዕዳውን አዳም ትንሣኤን ሰጥቶ ከሞት ሊያወጣው አልቻለም።

በመሆኑም ከበግና ከላም ከፍየልም የበለጠ መሥዋዕት ያስፈልገው ነበር።

<u>እግዚአብሔር ነውን?</u>

አዳምን ከምድር አፈር ያበጀው የሕይወት እስትንፋስንም የሰጠው እግዚአብሔር ነው። « አዳም ሆይ መሬት ነህና ወደ መሬትም ትመለሳለህ» ብሎ የፈረደበትም እግዚአብሔር ነው።

ሕያው አዳምን ሞት እንዲያሸንፈው ፍርድ የሰጠበትም እግዚአብሔር ነው። ስለዚህም ከመሬት ያበጀውን ወደ መሬትም የመለሰውን መልሶ ከመሬት ለማንሣት ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሕይወት ለሰጠው ሰው ሞት የፈረደበት መልሶም ከሞት ቀንበር አላቅቆ ሕይወት መስጠት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

የቀደመው ሰው አዳም በእግዚአብሔር ተፈጥሮ በእግዚአብሔር የከበረ ነበር። የዳነው አዳም ግን «በፍጡር የተፈጠረ» በፍጡር «የዳነ» በፍጡር «የከበረ» ቢሆን አዳም ወደ ጥንተ ክብሩ ተመለሰ፣ ፍጹም ድኅነትን አገኘ ማለት ባልተቻለ ነበር። ምክንያቱም የቀደመው አዳም በእግዚአብሔር ተፈጥሮ በእግዚአብሔር ክብሮ የሚኖር በመሆኑ ከኋለኛው አዳም ይበልጣል ያሰኛልና ነው።

እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥር ማንንም አላማከረም፣ ሲፈርድበትም የማንንም ሀሳብ አልጠየቀም። በመሆኑም እንዴት እንደፈጠረውም እንዴት እንደፈረደበትም ምሥጢሩን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሊያድነው ወደ ጥንት ክብሩ ሊመልሰው ዕውቀቱም ጥበቡም ሥልጣኑም ያለው እርሱ ብቻ ነው።

ለአዳም ቀዳሚቷን ሕግ የሰጠ እግዚአብሔር ነው። አዳም ሕጉን በጣሰ ጊዜ የቀጣው እግዚአብሔር ነው። ሁለተኛዋን ሕግ የመስጠት ሥልጣን ያለውም እግዚአብሔር ነው።

ስለዚህም አዳምን ሊያድነው ከወደቀበት ሊያነሣው ወደ ጥንት ርስቱ ሊመልሰው « አ አዳም አይቴ ሀሎከ» እያለ የመጣው መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው። ፍጡር አይደለም፣መልአክ አይደለም ነቢይ አይደለም /ምንም እንኳ ነቢይነት ገንዘቡ ቢሆን ለነቢያትም ሀብተ ትንቢትን የሚሰጠው እርሱ ቢሆን /

## እግዚአብሔር ለምን ሰው ሆነ?

ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው። ከፍጥረት መካከል አሟልቶ አጠናቆ ያወቀው ይመረምረው ዘንድ የሚቻለው የለም። መንፈስ ቅዱስ የገለጠላቸው አበው የነገሩንን እነሆ። . .

- እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር« ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳልነ» ብሎ ከምድር አፈር አበጀው ። ይህ በአብ ልብነት አሰበው፣ በወልድ ቃልነት ተናገረው፣በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት የፈጠሩት ሰው ቢወድቅ «ንግበር ሰብአ» ብሎ የተናገረው ቃል ወደ አዳም መጣ። ከመሬት ያበጀው እጅ/ክንድ/ ተዘረጋ።

- « ኦ አዳም መሬት አንተ ወትገብእ ውስተ መሬት» ብለው ሥላሴ በአብ ልብነት አሰበው በወልድ ቃልነት ፈረደው፣ በመንፈስ ቅዱስ ሕያውነት፣ አጽንተውት የኖሩትን ፍርድ ሊያነሣ የፈረደበት ቃል ወደ አዳም መጣ።

- ዓለም በኃጢአቱ ምክንያት የእግዚአብሔርን ድምፅ ፈርቶ ይኖር ነበር። ዘፍ 3÷10–13። እሥራኤል እግዚአብሔር በሲና ተራራ በተናገራቸው ጊዜ ሙሴን « አንተ ተናገረን፤ እኛም እንሰማለን፤ እንዳንሞት ግን እግዚአብሔር አይናገረን» ዘጸ. 20÷18 እንዳሉት። ይህን የኃጢአት ፍርኃት ከሰዎች ያርቅ ዘንድ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ከእኛ ጋር ተገኘ። /አማኑኤል / የሰው ቋንቋ እየተናገረ በሰው ሥርዓት ተመላለሰ። ድምፁን አሰምቶ በበለስ ሥር የተደበቀውን አዳም ፈለገው። አገኘውም።

- የሰው ልጅ በትእዛዛት የተሰጠውን ሕግ ይፈጽም ዘንድ አልቻለም፤ ሠርቶ ፈጽሞ አድርጎ ያሳየው የለምና። በመሆኑም እግዚአብሔር ወደኛ መጥቶ ሠርቶ አዲሲቷን ሕገ ወንጌልን ሰጠን።

  /የቀረውን መንፈስ ቅዱስ ይግለጥልን/

## እግዚአብሔር ሰውን እንዴት አዳነው?

አበው አግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል ይላሉ። ምክንያቱም ባሰቡት ቁጥር ኅሊናን የሚያስደንቅ ምሥጢር ተፈጽሟልና።

- የአዳምን ዕዳ ፍጡራን ሊከፍሉት አልቻሉም። እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ ዕዳችንን ከፈለልን። አዳም ሊቀበለው ይገባው የነበረውን ሁሉ ተቀብሎ አዳምን ነፃ አወጣው፤

- አዳም በበደሉ ከገነት ወደ ሲዖል ቢሰደድ፤ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ያለ በደሉ የገነት ምሳሌ ከሆነች ከነዓን የሲዖል ምሳሌ ወደሆነች ግብጽ ተሰደደ፤

- አዳም ከዓለመ መላእክት ተሰድዶ በእንስሳት መካከል ቢገኝ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በከብቶች በረት ተወለደ፤

- አዳም ከኅቱም መሬት ተገኝቶ ቢሳሳት መድኃኔዓለም ክርስቶስ ከኅቱም ድንግል ከእመቤታችን ተወልዶ አዳነው፤

- አዳም ከንጹሕ ምድር/መርገም ካልደረሰባት/ ተገኝቶ ቢሳሳት መድኃኔዓለም ክርስቶስ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ከሌለባት ከንጽሕት እመቤታችን ተወልዶ አዳነው፤

- አዳም የሠላሳ ዘመን ጐልማሳ ሆኖ ተፈጥሮ፣ ሰባት ዓመት በገነት ኖሮ፣ በምክረ ከይሲ ተታሎ ልጅነቱን ቢያጣ፣ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በሠላሳ ዓመቱ ተጠምቆ አዳነው፤

- አዳም በመብል ድል ተነሥቶ ከገነት ቢወጣ፤ መድኃኔዓለም ክርስቶስ «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም በእግዚአብሔር ቃል ጭምር እንጂ። ብሎ ፈቃደ ሥጋን ስስትን ድል ነሣለት»

- ዲያብሎስ አዳምን ከምድር ተለይታ በምትገኝ ገነት ለብቻው በመብል ድል ቢያደርገው ጌታም ዲያብሎስን ከከተማ ር ቃ በምትገኝ ገዳመ ቆሮንቶስ በጾም ድል ነሣው፤

- አዳም ሕግ ጥሶ ከጸጋ ቢራቆት መድኃኔዓለም ክርስቶስ ራቁቱን በመልዕልተ መስቀል ተሰቀለለት፤

- የአዳም እጅና እግር ወደ ዕፀበለስ ቢያመሩ የመድኃኔዓለም እጅና እግር በቅንዋት ተቸነከሩ፡

- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አምላክ ፣ ወልደእግዚአብሔር ፍጹም ካሣን ካሠልን። የአዳም ዐጽም ካረፈበት በጐልጐታ /ትርጓሜው የራስ ቅል ነው/ ተሰቅሎ ሞትን መውጊያ አሳጣው፤ የመ ቃ ብርም ኃይል ተሻረ። ርቀን የነበርነውን ልጆቼ አለን። /ማቴ 27÷33፣ 1ቆሮ 15÷56፣ /

የተዘጋች ገነት ተከፈተች፣ ዕድሜውን በሙሉ በኃጢአት ሲናውዝ ለነበረው ለፈያታዊ ዘየማን ታላቁ ብሥራት ተነገረው« «ከኔ ጋር በገነት ዛሬ ትሆናለህ» /ሉ ቃ 23÷43/ ገነት ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ተመልሰው በቀኙ ለሚቆሙ መከፈቷን አበሠረን:: ሞት በሞት ሞተ::

## «እግዚአብሔር ሰው ሆነ ስንል እንዴት ነው?»

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ነገረ ድኅነት ማለት የመዳን ነገር ማለት ነው:: በዚህ ምሥጢር ደግሞ ከዚህ ቀጥለን የምናየው የክርስቶስ ሰው የመሆን ምሥጢር /ምሥጢረ ሥጋዌ/ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል:: አንድ ሰው «አምላክ ሰው ሆነ» «እንዴት ሰው ሆነ?» የሚለውንም በደንብ መረዳት ይኖርበታልና:: እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በሥጋ ማርያም ስለመገለጡ ስንናገር በዙሪያው ማወቅ የሚገባን ብዙ ነገር አለ::

ቅድመ ዓለም ያለእናት ከባህርይ አባቱ ከአብ ድኅረ ዓለም ያለ አባት ከድንግል ማርያም በሥጋ የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን ነስቶ ሰው የመሆኑ ነገር ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ታላቅ ምሥጢር ነው /1ጢሞ 3÷16/:: ስለዚህ ይህን በሚገባ መረዳት አለብን:: ይህንን ስንል በራሳችን ተፈላስፈን እንመርምር ማለት አይደለም:: ነገር ግን ቅዱሳት መጽሐፍት በገለጡልን ዕውቀት መሠረት የሆነ እንዴት ሰው እንደሆነ እንረዳ ማለታችን እንጂ:: ጌታችን ጴጥሮስን «አንተ ዐለት ነህ በዚህ ዐለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ» ማቴ.16÷18 ያለው፣ የሃይማኖት መሠረት እምነት እንዳለው የተናገረለት፣ «አንተ መሲሁ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» ስላለ ነበር:: ማቴ.16÷16:: በፊቱ የቆመውን ወልደ አምላክ የአብ የባሕርይ ልጅ ብሎ በመጥራቱ ብፁዕ ተባለ::

ዛሬም ብዙዎች እንደሚሉት በተሳሳተ መልኩ ኢየሱስ ክርስቶስን የማይገባ ስም ሰጥተን ከመጥራት ተቆጥበን/ከስህተት ድነን/፣መለኮት ከሥጋ ፍፁም መዋሐዱን አምነን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ ነው፣ የአብ የባሕርይ ልጁ ነው ብለን ከአመን ያድነናል:: ስለዚህ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆነ ስንል በምን መልኩ? እንዴት? የሚለውንም ማወቅ አለብን:: ከዚህ ቀጥለን ይህን ሐሳብ መረዳት እንዲያስችለን አምላክ ሰው

የሆነው እንዴት እንደሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት በተጻፈውና አባቶች ባስተማሩን መሠረት እንመለከታለን።

በመለወጥ/ውላጤ/ ነውን? አይደለም፤ ለምን? ቢሉ መለወጥ ማለት ሥጋ ወደ መለኮትነት ወይም መለኮት ወደ ሥጋነት ተለውጧል፣ አንዱ በአንዱ ጠፍቷል ማለት ነው። ምሳሌ የሙሴ በትር ወደ እባብነት፣ የሎጥ ሚስት ወደ ጨው ዓምድነት እንደተለወጡ። ዘጸ 7÷8-13፣ ዘፍ 19÷26 አንድ ነገር ተለወጠ ስንል የቀደመ ባሕርይውን ለቆ ሌላ ይሆናል የሚል ትርጉም ይሰጠናል። የአምላክ ሰው የመሆን ምሥጢር ግን በመለወጥ አይደለም። ምክንያቱም መለኮት ወደ ሥጋነት ተለወጠ ካልን መለኮት የቀድሞ ማንነቱን ለቆ ሰው ብቻ ሆኗልና ዓለም አልዳነም ማለት ይሆንብናል። ይህ ደግሞ መለኮት ከሥጋ ጋር ስላልተዋሐደ ሥጋ ብቻውን ከሆነ መከራ መቀበሉ መሰቀሉ ሁሉ ለከንቱ ነው ያስብላል። በሥጋ ብቻ/በፍጡር ደም/ ዓለም አይድንምና።

በሌላ በኩል ሥጋ ተለውጦ መለኮትን ሆኗል በመለኮት ተውጧል ልንልም አንችልም። አምላክ ሰው ሆነ ካልን ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ መሆኑንም ከምረዳት ጋር መሆን አለበት። ምክንያቱም ሥጋ ባሕርይውን ለቅቆ ወደ መለኮትነት ተለውጧል ካልን አሁንም ዓለም አልዳነም ወደ ሚል ሀሳብ ስለሚወስድ ነው። ክርስቶስ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ ነው ብለን ካላመንን ሥጋ ተለውጧል ካልን መከራ የተቀበለው መለኮት ብቻውን ነው ያስብለናል። ይህ ደግሞ ስህተት ነው፤ መለኮት ሊዳሰስ፣ ሊሰቀል፣ሊቀበር አይችልምና። የግድ መከራን ለመቀበል የሥጋን ባሕርይ ባሕርይው ማድረግ ነበረበት። ስለዚህ በአጠቃላይ ስናየው ሥጋም ወደ መለ ኮትነት መለኮትም ወደ ሥጋነት አልተለወጡም በተዐቅቦ/በመጠባበቅ/ አንድ ሆኑ እንጂ። እግዚአብሔር በባሕርይው መለወጥ ስለሌለበት /ሚል 3÷6/ በሥጋ ባሕርይ ተለወጠ ማለት ስሕተት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም ዛሬም እስከ ዘለዓለም ያው ነው።/ዕብ 13÷6/

<u>በኅድረት ነውን? አይደለም።</u>

ይህ ሃሣብ የመጣው በምንታዌ /በሁለትነት/ ከሚያምኑና በ2ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከነበሩ መናፍቃን ነው። እነርሱም

ሁለት አምላክ አለን። አንዱ ክፉ ሌላው ደግ፤ ክፉው ይህን ዓለም /ሥጋን/ ፈጠረ፤ ደጉ የማይታየውን ዓለም /ነፍስን/ ፈጠረ። ስለዚህ ነፍስ በደጉ፡ ሥጋ በክፉ የተፈጠሩ በመሆናቸው ሁለቱ አይዋደዱም። ነፍስ በሥጋ ታስራ ስትስ ቋይ ትኖራለች፤ አምላክ እርሷን ነጻ ሊያደርግ መጣ። በሥጋ ላይ አድሮ ተመላለሰ፤ ግን ሥጋ አልተወሐደውም፤ ምክንያቱም ሥጋ የክፉ አምላክ የእጁ ሥራ የረከሰ ፍጥረት ነውና ይላሉ።

ይህ አስቀድሞ በነበሩ በሁለት አማልክት በሚያምኑ መናፍቃን የተጀመረ የኅድረት ትምህርት ሥር በስተመጨረሻ «በአንድ አምላክ እናምናለን» ወደሚሉ መናፍቃንም ደረሰ። ስለዚህም ከቤተክርስቲያን የተነሡ እነንስጥሮስም አምላክ ከድንግል ማርያም በተወለደው በኢየሱስ ላይ አደረበት እና የፀጋ አምላክ አደረገው እንጂ ሥጋን አልተዋሐደም አሉ። /ንስጥሮስ በ431 ዓ.ም በኤፌሶን የተወገዘ መናፍቅ ነው።/ ይህ መናፍቅ ዳዊት በማኅደሩ እንደሚያድር በማርያም ልጅ ኢየሱስ ላይ አምላክ አደረበት። ድንግል ማርያም የወለደችው ሰውን ነው።/ወላዲተ ሰብእ ይላታል/። ኋላ እርሷ በወለደችው ላይ ፈጣሪ አደረ ብሎ በድፍረት ያስተምር ነበር። ይህንን የክህደት ትምህርት ይዘው ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ነው። ሥጋን አልተዋሐደም የሚሉ መናፍቃን ዛሬም አሉ። ይህ ዓይነት አስተሳሰብ ግን ፍፁም ስህተት ነው። ምክንያቱም:–

ሀ. መናፍቃን እንደሚሉት እመቤታችን ሰውን ብቻ ወለደች ኋላ አምላክ መጥቶ አደረቦት ካልን ከፅንሰቱ ጀምሮ በልደቱ ጊዜ የተደረገውን ነገር የተነገረለትን ቃል መሻር ስለሚሆንብን ነው። ኢሳይያስ «ድንግል ትፀንሣለች፤ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» ኢሳ 7÷14 / አማኑኤል ትርጓሜውም «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው» ብሎ ተናግሯል። ማቴ 1÷23/ የተወለደው ሕጻን አማኑኤል የተባለው ሲወለድም አምላክ በመሆኑ ሥጋን ነስቶ ፍጹም ሰው መሆኑን ለመግለጥ ነበር። ከዚህ ሌላ አሁንም በትንቢት «ሕጻን ተወልዶልናልና÷ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ÷ የዘለዓለም አባት÷ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» የሚል ቃል እናገኛለን። ኢሳ 9÷6 በቤተልሔም ዋሻ ድንግል ማርያም የወለደችው ሰብአ ሰገል

ወርቅ ዕጣን ከርቤ መብአ አድርገው ያቀረቡለት ሕጻን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ስለሆነ ስሙም ኃያል አምላክ ተብሎ ይጠራል ተባለለት። ይህን ሕጻን ኤልሳቤጥ በማሕፀን ሳለ ገና ጌታዬ ብላ ጠርታዋለች። ሉቃ 1÷43። ስለዚህ መናፍቃን እንደሚሉት ድንግል ማርያም ወላዲተ ሰብእ/የሰው እናት/ አይደለችም። የአምላክ እናት እንጂ። ኢየሱስ ክርስቶስም አስቀድሞ ሰው የነበረ በኋላ በፀጋ የከበረ አይደለም። ከድንግል ማርያም ሥጋን ነስቶ ሰው የሆነ አምላክ እንጂ።

ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ነው፤ መለኮትና ሥጋ አልተዋሐዱም ከተባለ ሰው ገና አልዳነም ማለት ይሆናልና። በተዋሕዶ መለኮትና ሥጋ አንድ ካልሆኑ ኢሳይያስ«. . .በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕማማችንንም ተሸክሟል. . . ስለመተላለፋችን ቆሰለ ስለበደላችንም ደቀቀ. . . ተጨነቀ ተሰቃየ አፉን አልከፈተም» ኢሳ 53/ ብሎ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ባልተናገረ ነበር። እርሱስ በተዋሕዶ መለኮትና ሥጋ አንድ መሆናቸውን በመንፈስ ተገልጾለት ተናገረ። ለምን ቢሉ መታመምና መቸገር የመለኮት ባሕርይ አይደለምና፤ በተዋሐደው ሥጋ ታመመ፣ ተቸገረ ቆሰለ ለማለት። ሥጋ ብቻውን ነው ካልን ግን ሰው የራሱን መከራ ራሱ ተቀብሏልና ገና አልዳነም ወደሚል ክህደት ይወስዳል። ሰውም በሰው አይድንምና አዳም አልዳነም ማለትን ያስከትላል። በተዋሕዶ ምሥጢር ግን መለኮት የሥጋን ገንዘብ የራሱ በማድረግ ታመመ፣ ሥጋም የመለኮትን ገንዘብ የራሱ በማድረጉ መከራን ችሎ ታገሰና ተቀበለ፤ እንላለን። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ አይደለም። በመሆኑም ኅድረት የሚለው ቃል ክህደት ነው።

ሐ. እግዚአብሔር አብ ስለ ባሕርይ ልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የምወልደው የምወደው ልጄ እርሱ ነው በማለት መስክሯል። መለኮትና ሥጋ በተዋሕዶ አንድ ባይሆኑ ኖሮ በነቅዱስ ጴጥሮስ ፊት የቆመውን ኢየሱስ ክርስቶስን ልጄ ብሎ ባልጠራው በዚህም ፈንታ የልጄ ማደሪያ ባለው ነበር። ነገር ግን ሥጋ ከመለኮት ጋር በመዋሐዱ ማደሪያ ሳይሆን ልጄ ተብሎ ሥጋ የመለኮትን ገንዘብ ገንዘቡ አድርጎ የአብ የባሕርይ ልጁ ተባለ። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነው በኅድረት ሳይሆን በተዋሕዶ ነው።

በቱሳኤ ነውን? አይደለም።

ቱሳኤ ቅልቅል ማለት ነው። ይህም እንደ ማር እና እንደ ውኃ ነው፤ ውኃና ማር ሲቀላቀሉ ስም ማእከላዊ ይገኝባቸዋል። መልክ ማእከላዊ እንደ ማር ሳይነጣ እንደ ውኃ ሳይጠቁር መካከለኛ መልክ ይይዛል፤ ጣዕም ማዕከላዊ እንደ ማር ሳይከብድ እንደ ውኃም ሳይቀል መካከለኛ ጣዕም ይኖረዋል። ወተትና ቡናም ሲቀላቀሉ እንዲሁ ነው፤ ቡናው እንደ ወተት አይነጣም ወተቱም እንደቡና አይጠቁርም፤ መካከለኛ ቀለም ይኖራቸዋል።

በምሥጢረ ሥጋዌ ግን ሥጋና መለኮት አንድ የሆኑት ያለመቀላቀል ነው። ሥጋ ወደ መለኮትነት መለኮት ወደ ሥጋ ባሕርይ መጥቶ መካከለኛ የሆነ ነገር አልመጣም። ሥጋም ሥጋዊ ባሕርይውን ሳይለቅ መለኮትም መለኮታዊ ባሕርይውን ሳይተው በመጠባበቅ ተዋሕደዋል። ያለመቀላቀል ሌላ አዲስ ነገር ሳይፈጥሩ አንድ ሆነዋል። ሥጋም የመለኮትን ባሕርይ ገንዘቡ አድርጎ፣ መለኮትም የሥጋን ባሕርይ ገንዘቡ አድርጎ ተዋሕደዋል።

ምሳሌ፡- ሙሴ ባየት ዕፀ ሐመልማሉ ከነበልባሉ /ቅጠሉ ከእሳቱ/ ጋር ተስማምተው ነበር። አንዱ ሌላውን አላጠፋውም። ቅጠሉ እሳቱን ሳያጠፋ እሳቱ ቅጠሉን ሳያቃል ያለመጠፋፋት አንድ ላይ ታይተዋል። እንደዚሁም መለኮት የሥጋን ባሕርይ ሳያጠፋ ሁለቱ ያለመጠፋፋት አንድ ሆኑ። ከዚህ ውጭ ተቀላቀሉ ካልን ግን ከባሕርያቸው ለቀዋል፣ ክርስቶስ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ አይደለም፣ ሌላ አዲስ ባሕርይ አለው ስለሚያስብለን በሰውነቱ መብላት መጠጣቱን . . . የሰውን ሥራ መሥራቱን ምትሐት ነው እንድንል በአምላክነቱ ሙት ማስነሣቱን፣ ተአምር መሥራቱን፣ እንዳናምን እንድንጠራጠር ያደርገናል። በመቀላቀል ወደ ሌላ ባሕርይ ተቀይሯል ካልን ፍፁም አምላክ ነው ልንል አንችልምና ነው።

በትድምርት ነውን? አይደለም

ትድምርት መደረብ መደመር ማለት ነው። ይህም እንደ ልብስ እንደ እንጀራ ማለት ነው። ልብስ ቢደርቡት ይደረባል፣ ቢነጥሉት ይነጠላል፣ እንጀራም ቢደርቡት ይደረባል፣ ቢነጥሉት ይነጠላል። መለኮት ከሥጋ ጋር አንድ የሆነው ግን እንዲህ በመደረብ አይደለም፤ በተዋሕዶ እንጂ። ምክንያቱም

በትድምርት ከሆነ ሲፈልጉ መነጠል አለ። ቀድሞውንም በአንድ ላይ ይደረባል እንጂ አይዋሐዱም። መለኮትና ሥጋ ግን በመጀመሪያም በተዋሕዶ አንድ ሆነዋል ኋላም ያለመነጣጠል ኖረዋል። መለኮትን ከሥጋ ከተዋሐደ በኋላ መነጠል አይቻልም።

<u>በቡዐዴ ነውን? አይደለም።</u>

ቡዐዴ መለየት መለያየት ማለት ነው። ሁለት ነገሮች አንድ ላይ ከሆኑ በኋላ መለየት መነጠል ሲቻል ቡዐዴ ይባላል። ለምሳሌ፤ በቆሎና ስንዴን/በጥሬአቸው እነዚህ ሁለት የእህል ዘሮችን ከቀላቀልናቸው በኋላ ስንፈልግ መለየት እንችላለን። አብረውም ሳሉ በቆሎውን በቆሎ ስንዴውን ስንዴ እንላለን። የክርስቶስ ሰው የመሆን ምሥጢር ግን ከዚህ የተለየ ነው። ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋና መለኮትን ለያይቶ ለየብቻ ይህ መለኮት ነው ይህ ሥጋ ነው አይባልም። እንደ ብረትና እሳት ፍፁም ተዋሕዶ ስለሆነ መነጣጠል አይቻልም። ስለዚህ ክርስቶስ ሰው የሆነው እንበለ ቡዐዴ ነው።

<u>በተዋሕዶ ነውን? አዎን።</u>

በተዋሕዶ ነው። ተዋሕዶ ከሚጠት፣ ውላጤ፣ ቱሳኤ፣ ትድምርትና ቡዐዴ የተለየና አምላክ ሰው የሆነበትን ምሥጢር የሚገልጥ ቃል ነው።

ሁለት አካላት አንዱ አንዱን ሳያጠፋ ሳይለውጠው፣ያለመቀላቀል ያለመደራረብ/በተዐቅቦ/ በመጠባበቅ አንድ ሲሆኑ ተዋሕዶ ይባላል።

<u>ለምሳሌ፤</u> የብረትና የእሳት ውሕደት /አንድነት/። ብረትና እሳት ሲዋሐዱ ብረት የእሳትን ገንዘብ ገንዘቡ ያደርጋል። አስቀድሞ የማያ ቃ ጥል የነበረው ኋላ ማ ቃ ጠል መፋጀት ይጀምራል። የእሳቱን ብርሃን ወርሶ የሚያበራም ይሆናል። እሳትም የብረትን ባሕርይ ባሕርይው ያደርጋል። በቀደመ አኗኗሩ ቅርፅ የሌለው ሲሆን ኋላ ከብረት ሲዋሐድ የብረቱን ቅርፅ ወርሶ ቅርጽ ያለው ይሆናል። አስቀድሞ የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ፣ የማይመታው ኋላ ብረቱን በመዋሐዱ መጨበጥ መዳሰስ መመታት ይጀምራል።

እንደዚሁ ሁሉ መለኮት አስቀድሞ እንደቀድሞ በአኗኗሩ ረቂቅ ሲሆን ነገር ግን እሳት ብረቱን ተዋሕዶ እሳትነቱን እንደሚታይ እርሱም ሥጋን ተዋሕዶ በግዘፍ ታየ፣ ተገለጠ፡፡ እሳት ከብረት ጋር ሆኖ በመዶሻ እንደሚመታ ነገር ግን መዶሻው ባሕርይውን እሳትነት እንደማያናውፅበት ሁሉ መለኮትም ከተዋሕደው ሥጋ ጋር በአንድነት በመኖሩ አብሮ መከራን ተቀበለ ሞቶ ተቀበረ፡፡ ይህ ግን መለኮታዊ ባሕርይውን አላገኘውም/በመለኮት አልሞተም /በለበሰው ሥጋ እንጂ በሌላ በኩል ብረቱም አስቀድሞ የሌለው የማ ቃ ጠል ባሕርይ ከእሳት ወርሶ እሳት ይሆናል፡ ያ ቃጥላል፡፡ በዚህ ዓይነት ደካማ የነበረ ሥጋ ከመለኮት ጋር በተዋሕዶ ሞትን ድል የሚያደርግ ተአምራትን የሚሠራ ሆነ፡፡ ይህ ቅዱስ ቄርሎስ ስለ መለኮት የመሠለው ምሳሌ ነው፡፡

ይኸው አባት በሌላ ሥፍራ ለተዋሕዶ ምሳሌ እንዲሆን የነፍስንና የሥጋንም ተዋሕዶ ያነሳል፡፡ «የሚረዳህስ ከሆነ የትስብእትና /የሥጋና/ የመለኮትን ተዋሕዶ በእኛ ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ መሰልን እንነግርሀለን፡፡ እኛ በነፍስ በሥጋ የተፈጠርን ነንና አንዱን የሥጋ አንዱን የነፍስ ብለን ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ አናደርገውም፡፡ ሰው ከሁለት አንድ በመሆኑ አንድ ነው እንጂ፡፡ ከሁለቱ ባሕርያት አንድ በመሆኑ ሁለት ሰው አይባልም፡፡ በነፍስ በሥጋ የተፈጠረ ሰው አንድ ነው እንጂ፡፡ ይህንንስ ካወቅን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተዋሕዶ በፊት እርስ በርሳቸው አንድ ካልነበ ሩ ከተዋሕዶ በኋ ላም ከማይለያዩ ከሁለት ባሕርያት አንድ እንደሆነ እናው ቃን፡፡ /ሃይ.አበ.ዘቄርሎስ 78÷19/፡፡

በእነዚህ ሁለት ምሳሌዎች እንደተመለከትነው ሁለት የተለያዩ ባሕርያት ያላቸው አካላት ተዋሕደው ያለመለያየት ያለመጠፋፋት አንድ ባሕርይ ስለሆኑ ተዋሐዱ ይባላል፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ/ሥግው ቃል/ሥጋን የተዋሐደ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ከተዋሕዶ በኋላ መለያየት አንችልም፡፡ ይህ የመለኮት ነው ይህ የሥጋ ነው፣ አይባልም፡፡ ሁለቱ በፍፁም ተዋሕዶ አንድ ሆነዋልና፡፡

ለምሳሌ፡- ጌታችን የሠራቸው ተአምራት ለዚህ ማስረጃ ይሆኑናሉ፡፡ ዓይነ ስውሩን በምራቁ አፈር ለውሶ በመቀባት አዳነው፡፡ ምራቅ የሥጋ ገንዘብ የነበረ ተአምር የመሥራት ኃይል ያልነበረው ሲሆን፤አሁን ግን ሥጋ ፍፁም ከመለኮት ጋር ተዋሕዷልና ጌታችን በምራቁ ዓይን አበራ፡፡ ይህን ዓይተን

ተአምር የሠራው በሥጋው ነው፣ በመለኮት ነው፣ ብሎ መነጣጠል አይቻልም:: ጌታችን ከሐዋርያት ጋር በታንኳ ሲጓዝ አንቀላፋ:: ጌታ ሆይ ጠፋን ብለው ቀሰቀሱት:: ተነሥቶም ነፋሱን ገሠፀው:: እዚህ ላይ ከሥጋ ጋር የተዋሐደ መለኮት ሥጋ ሲያንቀላፋም አለ:: መለያየት የለባቸውም:: ጌታ ተነሥቶ ማዕበሉን ገሠፀ:: ከላይ እንዳየነው ማንቀላፋት የሥጋ ባሕርይ ነውና ተኛ:: በመቀጠል ተነሥቶ ማዕበሉን ፀጥ አደረገው:: ባሕር መገሠፅ ፍጥረታትን ማዘዝ የመለኮት ባሕርይ በመሆኑ ይህ ይህንን አደረገ እያሉ መለያየት አይቻልም:: የተኛውም ተነሥቶ ማዕበሉን ፀጥ ያደረገውም አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው በመሆኑ ይተኛ፣ ይበላ፣ ይጠጣ፣ ተአምር ይሠራ፣ ሙት ያስነሣ ነበር::

ጌታችን ኢየሲስ ክርስቶስ ሥጋን ነስቶ ሰው የሆነ አምላክ ነው ስንል ሰው በመሆኑ በባሕርይው ተዋራጅነት የለበትም:: በሰማይ በዙፋኑ እየተመሰገነ በምድር ዞሮ አስተማረ መከራን ተቀበለ እንጂ:: ቅዱስ ያሬድ ስለዚህ «ፍጥረቱን ሁሉ የሚመግብ ጌታቸው በብትሽ/በክንድሽ/ ተቀምጦ እንደ ሕጻን ጡትሽን ሲጠባ ባዩት ጊዜ በአርያም ፈለጉትና በዚህ ዓለም እንደ ቀድሞው ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አገኙት::/ይህን ያዩ መላእክት ናቸው/ ፀሐይ ባለችበት ሆና ምድርን እንደምታሞቅ እርሱም በዙፋኑ ተቀምጦ /አለምን እየገዛ/ በምድር በሥጋ ማርያም ተገለጠ ሥጋን ተዋሕዶ ዞሮ አስተማረ::

በአጠቃላይ ስንመለከት ተዋሕዶ ማለት እንደ አውጣኪ ተጣፍቶ አንድ ባሕርይ ብቻ ሳንል እንደንስጥሮስ በመደረብ ሁለት ባሕርይ ነው ሳንል እንደ ሌሎች መናፍቃን በመቀላቀል. . .የሚል ሀሳብ ሳናስገባ መለኮት ከሥጋ ጋር ፍፁም በመዋሐዱ የኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ መሆኑን የምንመሰክርበት ነው::

ለመሆኑ ጌታችን በተዋሕዶ ሰውን ያዳነው ለምንድን ነው? ቅዱስ አትናቴዎስ እንደተናገረው::

ሀ. ሞት ከእኛ ጋር ተዋሕዶ ይኖር ነበርና ሞትን ይሽረው ይነቅለው ዘንድ መለኮት ከእኛ ሥጋ ጋር ተዋሐደ::

ለ. ዲያብሎስ በእባብ ሥጋ ተሰውሮ አዳምና ሔዋንን አሳስቷቸው ነበርና:: መለኮትም የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ ድል

ነሳው:: ምሥጢርን በምሥጢር መመለስ የእግዚአብሔር ጥበብ ነውና::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ያስተምር በነበረበት ወቅት ሙት ያስነሣ፣ ድውያንን ይፈውስ፣ ማዕበሉን ይገሥፅ ነበር:: እነዚህ በፍጡር ሊሠሩ የማይችሉ ናቸው:: እርሱ አምላክ ስለሆነ አድርጓቸዋል:: በሌላ በኩል ይራብ፣ይጠማ፣መከራ ይቀበል ነበር:: አምላክ የማይራብ የማይጠማ መከራ የማይቀበል ነው:: እሱ ግን ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው ነውና ይህንን በፍ ቃሉ አድርጎታል:: ይህንን ለይተን እዚህ ላይ አምላክ ነበር:: በዚህ ቦታ ሰው ሆነ አንልም:: ይልቅስ ወልደ አብ ወልደ ማርያም/የአብ ልጅ የማርያም ልጅ/ ሥግው ቃ ል ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው በመሆኑ ይህን አደረገ እንላለን እንጂ:: እሱ በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ በመሆኑ የሥጋንም የመለኮትንም ሥራ ሠራ:: በእርሱ ባሕርይ ተከፍሎ መለያየት የለበትም::

ስለ ጌታችን ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር:: «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ...» ይላል:: ሐዋ 20÷28:: መለኮት በባሕርይው ሥጋና ደም ያለው አይደለም ረቂቅ ነው እንጂ:: ነገር ግን የሥጋን ገንዘብ ገንዘቡ አድርጎ ከሥጋ ጋር ፍፁም ተዋሕዷልና እግዚአብሔር ደሙን አፈሰሰ ተባለ:: ከተዋሕዶ በኋላ መለኮትን ለብቻ ሥጋን ለብቻ መነጠል ስለማይቻል ይህ ተናገረ::

## ነገረ ማርያም በነገረ ድኅነት

ቤተክርስቲያናችን ለምን ስለእመቤታችን ዘወትር እንደምታስተምር አንዳንድ ሰዎች ግር ሲላቸው ይታያል:: እንዲያውም «አላዋቂ ሳሚ...» እንዲሉ ስለ እመቤታችን ማስተማሯ ስለ ጌታችን እንዳታስተምር አድርጓታል ብለው የሚናገሩም አሉ:: ቤተክርስቲያናችን ግን ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የምታስተምረው ለርሷ ካላት ልዩ ፍቅር ብቻ ወይም ስለጌታችን የምታስተምረው አልቆባት አይደለም:: ምክንያቱም ከኢትዮጵያ ሊቃውንት በላይ ለነገረ መለኰት ምሁርና ጥንቁቅ ከማግኘት የሰማይን ስፋት ልክ ማግኘቱ ሳይቀል አይቀርም::

በቅዳሴያችን፣ በዘወትር፣ ጸሎታችን፣ በመዝሙራችን፣ በሥርዓታችን፣ በትውፊታችን፣ በአለባበሳችን ሳይቀር የነገረ ድኅነት ትምህርት የሌለበት የለም:: ሰዎች ዐረፍተ ዘመናቸው ደርሶ

ወደመ ቃ ብር ሲሸኙ በምናደርገው ጸሎተ ፍትሐት ለክርስቲያኑ በሚደረገው የቀብር ሥነሥርዓት ሁሉ ነገረ ድኅነት ይሰበካል ይገለጣል።

ቤተክርስቲያን ነገረ ማርያምን ዘወትር ለምእመናን የምታስተምረው ከነገረ ድኅነት ጋር የተያየዘ ጥልቅ ምሥጢር ስላለው ነው። ነገረ ድኅነትን ለመማር ለመረዳትና ለማመን ነገረ ማርያም መሠረት፣ መቅድም ነው። ያለነገረ ማርያም ነገረ ድኅነትን፣ ያለመሠረት ቤት ማለት ነው። እስቲ ለዚህ ምሥክር የሚሆኑ ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት።

1. የሔዋን ካሣ

ሀ. እናታችን ሔዋን ምክንያተ ስህተት፣ ምክንየተ ሞት በመሆኗ ፍዳ መርገም ደርሶባት ነበር። ያበላችን ፍሬ ሞትን የሚያመጣ ከገነት የሚያስወጣ በመሆኑ ትውልድ ሁሉ ሲወቅሳት ይኖር ነበር።

ዳግማዊት ሔዋን እመቤታችን ግን ምክንያተ ድኂን ሆነች። የሰጠችን ፍሬ ሞትን የሚያመጣ ሳይሆን ተበልቶ ተጠጥቶ የዘላለምን ሕይወት የሚያስጥ ነው።/ዮሐ 6÷36/ ትውልድ ሁሉ ሔዋንን ሲወቅስ ኖረ። እመቤታችንንግን ትውልድ ሁሉ ያመሰግናታል። /ሉ ቃ 1÷48/ ሶሪያዊው ቅዱስ ኤፍሬም በሐሙስ ውዳሴው «... ስለ ሔዋን የገነት በር ተዘጋ ዳግመኛም ስለ ድንግልማርያም ተከፈተልን። ከዕፀ ሕይወት እንበላ ዘንድ አደለን። » ብሏል

ለ. ሔዋን በዲያቢሎስ ተመክራ ኃጢአትን ጸነሰች። ሞትንም ወለደች። እመቤታችን ግን በሊቀመላእክት ቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ሕይወትን ፀነሰች ትንሣኤን ወለደች። /ሉ ቃ 1÷28-38/

በሴት የመጣ ሞት በሴት ድል ተመታ።«እመቤታችንን የሔዋን መድኃኒቷ» ያሰኛትም ይኼው ነው። ይኼንን ድንቅ ምሥጢር ካልተረዳንና ካላመንን ሔዋን መካሥዋን የሴቶች ክብራቸው መመለሱን በምን ተረድተን እንዴትስ ልናምን እንችላለን?

## 2. የአዳም ካሣ

ሀ. አዳም የተወለደው ከኀቱም ምድር ነው። ምድር ከአዳም በፊትም ሆነ በኋላ ሌላ ልጅ የላትም። አዳምንም ያስገኘችው በጥበበ መንፈስ ቅዱስ በፈቃደ ሥላሴ እንጂ ዘር አላስፈለጋትም። ያ በዚህ ግሩም ድንቅ ምሥጢር የተገኘ አዳም ግን ሞትን በራሱ ላይ በማምጣቱ ወደቀ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትም አንዱና ዋነኛው ምክንያት ለቤዛ ዓለም፣ ለካሣ ዓለም ነው። ይኸንንም በመዋዕለ ሥጋዌው በሠራው ሥራ ሁሉ ገልጦታል።

ጌታችን ሲወለድ ያለወንድ ዘር፣ በግብረ መንፈስ ቅዱስ በኀቱም ድንግልና ከእመቤታችን ነው። የእመቤታችንን ድንግልና ካልተቀበልን የመጀመሪያው አዳም ከኋለኛው አዳም ይበልጣል ማለት ነው። ያነሰው ደግሞ የበለጠውን ሊያድን እንዴት ይቻለዋል? ለእኛስ እንዲህ አናምንም ከኀትምት ምድር ተወልዶ የወደቀውን አዳም ያነሣው ዘንድ ያለወንድ ዘር ከድንግል ማርያም ተወለደ። ምድር ከአዳም በፊትም ሆነ በኋላ ሌላ ልጅ እንዳላስገኘች እመቤታችንም ከጌታችን በፊትም ሆነ በኋላ በድንግልና ኖረች። በዚህም ዘላለማዊ ድንግል ትባላለች። ልበ አምላክ ዳዊት ይኼንን በምሳሌ ሲያስረዳን።

«እውነት ከምድር በቀለች
ጽድቅና ሰላም ተስማሙ»

ብሏል መዝ 84÷10–11። እውነት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። /ዮሐ 14÷7/ እውነት የበቀለባት ምድር ደግሞ እመቤታችን ናት። ጽድቅና ሰላም የተስማሙትም በልደተ ክርስቶስ ነው።

ለ. አዳም የተገኘው መርገም ካልደረሰባት ምድር ነው። ምድር መርገምን ያመጣችው በልጅዋ በአዳም በደል ነው። አምላክን የወለደች ቅድስት ድንግል ማርያምም በደል መርገም ያልደረሰባት ንጽሕት ቅድስት ናት። አስቀድማ በደል /ጥንተ አብሶ/ ነበረባት ካልን ከኋለኛው ምድር የቀደመችው ትበልጣለች ያሰኝብናል። ይኸ ከሆነ ደግሞ አዳም ተዋጀ፣ ተካሠ ወደ ክብሩ ተመለሰ ማለት አይቻልም። ያነሰው የበለጠውን ሊያከብረው አይችልምና። ስለዚህም ቤተክርስቲያናችን እመቤታችን የአዳም ኃጢአት ያልደረሰባት ናት ብላ

የምታስተምረው ርቱዕ እንደሆነ በዚህ ይታወ ቋል። እምነቷ ከእምነቷ እንደሌሎቹ አይጣላምና። የሌሎቹ ግን የሚናገሩትም ሆነ የሚጽፉት እርስ በርሱ የሚጋጭ ነው።

አንዳንዶች እመቤታችን «ከአዳም ኃጢአት የነጻችው በብሥራተ ገብርኤል ነው።» ይላሉ። ይህ ከሆነማ የክርስቶስ መሞት ለከንቱ ሆነ ያሰኝባቸዋል። ብሥራተ መልአክ ከቀደመ ኃጢአት /ከጥንተ አብሶ/ ነጻ የሚያወጣ ቢሆን ኖሮ በብሉይ እነ ብእሲተ ማኑሄ/መሳ 13÷1–20/ በሐዲስ ደግሞ እነ ዘካርያስ /ሉ ቃ 1÷13–20/ ከዚህ ቀንበር ነፃ በወጡ ነበር። በብሥራት ልጅ አግኝተዋልና። በሌላ በኩልም የመልአክ ብሥራት ከጥንተ አብሶ ለመላቀቅ ካስቻለ እልፍ አእላፍ መላእክት ተልከው አዳምን ከነዘሮቹ ባዳኑት ነበር። የቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ከጥንተ አብሶ ካላቀቀ ከክርስቶስ ሞት ጋር እኩል ነው ማለት ነው /ሎቱ ስብሐት/። እኛስ እንዲህ አንልም ይህ ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው የሃይማኖት ስሕተት ያስከትላል።

3 <u>የሕያዋን እናት</u>

አዳም ለሚስቱ የሕያዋን እናት ብሎ ስም አውጥቶ ነበር። ሔዋን ማለት የሕያዋን እናት ማለት ነው።/ዘፍ 3÷20/ ነገር ግን የሕያዋን እናት በርግጥ አልነበረችም። እርስዋም ልጆችዋም የሞት ባሮች ነበ ሩና።«ከአዳም እስከ ሙሴ ሞት ነገሠ» እንዲል። ሮሜ 5÷19። ታዲያ የሕያዋን እናት ማንናት?

የሰው ልጅ በጥፋቱ እናትም አባትም አጥቷል። አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን ከገነት ተባረ ሩ ለኛ ቤዛ መከታ፣አለኝታ ሊሆኑ ቀርቶ ለነርሱም አስፈልጓቸው ነበር። በዚህም ምክንያት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአዳም ተገብቶ በሥጋ ብዕሲ መጣ። ወንዶቹ «እኛ ብቻ ተክሰን የሔዋን ነገር ግን መናቀረ» እንዳይሉ እመቤታችንን መርጦና ቀድሶ አዘጋጀ። አባትም እናትም ያጣው የሰው ዘር አባት አገኘ።«አባ አባት ብለን የምንጠራበት የልጅነት ጸጋ ተሰጠን» እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ «አባታችን ሆይ» በሉ የተባልነውም ይኸ ክብር ስለተመለሰልን ነው። ስለሔዋን ደግሞ የሕያዋን እናት ትሆነን ዘንድ እመቤታችንን አገኘን። የሰው ልጅ ገነትንም እናቱንም ያጣው ባንድ ጊዜ እንደነበር ሁሉ ገነትንም እናቱንም ያገኘው ደግሞ በአንድ ጊዜ ነው። እመቤታችን በጸሎታችን ብዛት፣በቅድስናችን ብ ቃት

ያገኘናት ሳትሆን ስለምታስፈልገን የተሰጠችን እናት ናት። ይህም ጌታችን በመልዕልተ መስቀል የሚወደውን ደቀመዝሙሩን ቅዱስ ዮሐንስን «እነኋት እናትህ» ባለው ጊዜ ታውቋል።/ዮሐ 19÷19/ ነቢዩ ዳዊትም አስቀድሞ «ሰው እናታችን ጽዮን ይላል» ሲል ተናግሮላት ነበር። መዝ 86÷5።

አማናዊቷ ሔዋንም /እመሕያዋን/ እመቤታች ናት። ልጇ ሞትን አሸንፎ እኛ ልጆቿ የምናሸንፍበትን ሥልጣን እንደሰጠን እርሷም ሞትን አሸንፋዋለችና። እንዲህ እናምናለን እንዲህም እንመሰክራለን። ያለበለዚያ ግን የሰው ልጅ ወደጥንተ ክብሩ ተመለሰ ፍጹም ድኅነትን አገኘ ለማለት አንችልም።

እንግዲህ በነዚህ ጥቂት ምሳሌዎች ነገረ ማርያም ለነገረ ድኅነት ምን ያህል መሠረት እንደሆነ ተመልክተናል። ነገረ ማርያምን በሚገባ ያልተረዳና ያልጠነቀቀ ነገረ ድኅነትንም ሆነ ነገረ መለኮትን ጠንቅቆ መረዳት አይቻለውም። ከመሠረቱ አንድ ድንጋይ በተነሣ ቁጥር ቤቱም የዚያን ያህል እንደሚናጋ በነገረ ማርያም አንዳች ስህተት ብንጨምር የነገረ መለኮት ትምህርታችንም ሆነ እምነታችን የዚያኑ ያህል የተሳሳተ ይሆናል። ያለ ንጽሕት ሃይማኖት ደግሞ ንጽሕና አይገኝም።

ቤተክርስቲያናችን ነገረ ማርያምን አዘውትራ የምታስተምረው ያለጥርጥርና ያለነቀፋም የምታምነው ለድኅነት መሠረት መሆኑን በተረዳ ነገር ስላወቀች ነው። በሥዕሎቻችን፣ በጸሎታችን፣ በመጻሕፍቶቻችን፣ በዝማሬዎቻችን፣ በሥርዓታችንና በትውፊታችንም ስለእመቤታችን የሚነሣው ለዚህ ነው። ሕገ እግዚአብሔርን አምዘግዝገው ጥለው «ድኅነት የሚገኘው በጸጋ ብቻ ነው» ይላሉ። ይህ ግን የእግዚአብሔርን ቃሉና ትዕዛዝ የሚቃወም የሐሰት ትምህርት ነው።

## በነገረ ድኅነት ውስጥ የሰው ልጅ ድርሻ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር ሰውን በአርአያውና በምሳሌው /የሚያስብና የሚያስተውል አድርጎ/ከፈጠረው በኋላ «ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፣ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» የሚል«ትእዛዝን» ሰጥቶ በገነት አኖረው። ይህ«ትእዛዝ» ከሁለቱ አንዱን የመምረጥ የውዴታ ግዴታ ትእዛዝ እንጂ ብዙ ጊዜ እንደምናውቀው ይኽን ሳይሆን ያኛውን

አድርግ ዓይነት ትእዛዝ አይደለም። እግዚአብሔር «በገነት መካከል የሕይወትን ዛፍ÷መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውንም ዛፍ» ሲያበቅል አስቀድሞ የሰውን ልጅ የሚያስብና የሚያስተውል አድርጐ ፈጥሮት ነው። ከዚህም የተነሣ ክፉውንና ደጉን ማወቅ በሚችልበት አእምሮው ተጠቅሞ የሕይወትን ዛፍ /ዕፀ ሕይወት/ ወይም ሞት የምታመጣዋን ዛፍ /ዕፀ ሞት/ መርጦ የመብላት ነጻፈ ቃድ አለው።

በመሆኑም ነጻ ፈ ቃድ ማለት አንድ ሰው አንድን ድርጊት ለመፈጸም ወይም ላለመፈጸም ያለው የፍላጐት ነጻነት ነው። በዚህ ነጻነት በመጠቀም ሊያስመሰግን ወይም ሊያስወቅስ፣ ዋጋ ሊያሰጥ ወይም ለ ያስቀጣ፣ ሊጐዳ ወይም ሊጠቅም የሚችለውን አድራጐት ለማድረግም ሆነ ላለማድረግ ይችላል። አንድን ድርጊት የሚያደርገው ወይም የማያደርገው ማንም ሳያስገድደው በፍላጎቱ ነው። የነጻ ፈ ቃዱም ውጤት እንደምርጫው ሕይወት ወይም ሞት ሊሆን ይችላል። ይኸንን በተመለከተ በኦሪቱ «ተመልከት ዛሬ በፊትህ ሕይወትና መልካምነትን÷ሞትንና ክፋትን አኑሬልሃለሁ» ተብሏል። ዘዳ 30÷15

በሰው ልጅ ድኅነት ውስጥ የእግዚአብሔር ድርሻ እንዳለ ሁሉ የሚድነውም ሰው ለድኅነቱ የሚያበረክተው ድርሻ አለ። እግዚአብሔር በደሙ ፈሳሽነት ዕዳችንን ከፍሎ ከዘላለም ባርነትና ሞት ነጻ አውጥቶናል። ለመዳን ነጻነትን ሰጥቶናል እንጂ አላስገደደንም። በዚህ ነጻ ፈ ቃድ እንደ ይሁዳና ዴማስ ያሉ ሲጐዱበት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታትና ቅዱሳን ግን ተጠቅመውበታል፤ ድነውበታልም።

ድኅነት በነገረ መለኮት ትርጉም በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምኖ እርሱ ያስተማረውን ትምህርት በሕይወት በመተርጐም የሚገኝ የዘላለም ሕይወት ነው። ጌታችን በመዋዕለ ትምህርቱ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል» ዮሐ 3÷16–18 በማለት እንዳስተማረው።

ለመሆኑ በነገረ ድኅነት ውስጥ የሰው ልጅ ድርሻ ምንድን ነው? ይኸንን ጥያቄ የምንመልሰው የሰውን ልጅ የመዳን ነጻ ፈቃድ የመጠቀም መብቱን በመያዝ ነው። ሰው ከዘላለማዊ ጥፋት ይድን ዘንድ ሊያደርገው የሚገባውን ሁሉ በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣችን 2ኛ ዓመት ቁጥር 4፤3ኛ ዓመት ቁጥር 1ና 3ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት በስፋት የዘረዘርናቸው ቢሆንም ዋና ዋና የምንላቸውን መርጠን በአጫጭሩ እንደ ሚከተለው ለማቅረብ እንሞክራለን።

## ሃይማኖት

ሃይማኖት የሚለው ቃል ሰፊ ሐተታ ያለው ቢሆንም ባጭር ቃል ስንጠቀልለው ለዚህ ዓለም ሠራዒ መጋቢ አለው፤ ይህም አምላክ በአንድነትና በሦስትነት የሚመለክ እግዚአብሔር ነው ብሎ ማመን ነው። እግዚአብሔር በአንድነትና በሦስትነት ያለ፤ የሚኖር በመሆኑ ለመዳን የሚሻ ሁሉ የሥላሴን ሕልውና ማመን ግዴታው ነው።

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ማለትም በሥላሴ አንድነትና ሦስትነት የማያምን ሁሉ ከእውነተኛ እምነት የወጣ ነው። ዮሐ 14÷1። ዮሐ 17÷3። ዮሐ 14÷15–17። 2ቆሮ 13÷14። ዮሐ 15÷26 ዮሐ 1÷14።

ስለዚህ ቤት ያለመሠረት ሊቆም እንደማይችል ሁሉ የዘላለማዊ ድኅነት መሠረትም ሃይማኖት/እምነት/ ነው። ሃይማኖት የድኅነት መሠረት ነው ስንል በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ማመን፤ ሥላሴ በአካል ሦስት በመለኮት አንድ ብሎ ማመን፤ ሲሆን ከንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ የተወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ነው፤ ድንግል ማርያምም ወላዲተ አምላክ ናት ብሎ ማመን መታመን ነው። እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሁለቱ ትምህርቶች በቤተክርስቲያናችን ምሥጢረ ሥላሴና ምሥጢረ ሥጋዌ ይባላሉ። አንድ ሰው ደግሞ ለመዳን በእነዚህ ማመን አለበት።

## ጥምቀት

ጥምቀት የድኅነት በር ከፋች ነው። ጌታችንም የጥምቀትን የድኅነት በር ከፋችነት በመዋዕለ ትምህርቱ ሲያጠይቅ «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት

ሊገባ አይችልም» ብሏል፡፡ ዮሐ 3÷5፡፡ ከውኃና ከመንፈስ መወለድ ማለት ምሥጢረ ጥምቀትን መፈጸም ማለት መሆኑ አያከራክርም፡፡ በሌላም ቦታ ጌታ ራሱ«ያመነ የተጠመቀ ይድናል» በማለት በሃይማኖት የተመሠረተ ሰው ሃይማኖቱን በጥምቀት ማጽናት እንዳለበት አስተምሯል፡፡ ማር16÷16፡፡

ከየሀገሩ የእሸት በዓልን ለማክበር በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ለነበሩ አይሁድ ቅዱስ ጴጥሮስ የዘላለም ሕይወትን ይወርሱ ዘንድ ሲያስተምራቸው በትምህርቱ ልባቸው ተነክቶ«ምን እናድርግ?» ብለው ለጠየቁት ጥያቄ ይድኑ ዘንድ መጠመቅ እንዳለባቸው ሲያስረዳቸው «ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ...» ነበር ያላቸው፡፡ ሐዋ 2÷38፡፡

ይድኑ ዘንድ የሐዋርያትን ትምህርት ሰምተው በጌታ አምላክነት ያመኑ፣ ልድያ፣ቆርነሌዎስ፣ የወኅኒ ጠባቂው ሁሉ ተጠ ምቀዋል፡፡ የሐዋ 10÷47፡፡ የሐዋ 16÷15 እና 33፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ይድን ዘንድ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሊጠመቅ ይገባዋል፡፡/ማቴ 28÷19–20/

## <u>ቅዱስ ቁርባን</u>

መንግሥተ እግዚአብሔር ያለ ሥጋ ወደሙ አትወረስም፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውን በልተን፣ ክቡር ደሙን ጠጥተን እንድን ዘንድ በማያልፍ ቃሉ አስተምሮናል፡፡ «ኅብስቱን አንሥቶ ባረከ ቆርሶ ለደቀመዛሙርቱ ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ፡፡ ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡» ማቴ 26÷26–29፡፡

ይህ «ሥጦታ» ከአምላክ ዘንድ ነውና የሰው ልጅ ሊድን ቢወድ ሊቀበለው ግዴታው ነው፡፡ ይህንንም ራሱ ባለቤቱ በ ቃሉ ነግሮናል፡፡ «እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙን ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፡፡ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ፡፡ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ነውና፡፡ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፡፡ እኔም

በእርሱ እኖራለሁ:: ዮሐ 6÷32–57:: ጌታችን «ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜ እውነተኛ መጠጥ ነው» በማለቱም ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ለመታሰቢያ ሳይሆን ድኅነት የሚገኝበት አማናዊ የሕይወት እንጀራነቱን ያስረዳል::

## መልካም ምግባር

ሃይማኖት ያለምግባር ምግባር ያለ ሃይማኖት እያንዳንዱ ለየብቻው ምንም ዓይነት ፋይዳ እንደማይፈይድ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ ገልጾታል:: ያዕ 2÷26:: ስለዚህ ሕይወት የሚገኝበት ሃይማኖት ምግባር አልባ አይደለም:: ከምግባር ጋር የተቀናጀ ነው እንጂ:: ሃየማኖትና ምግባር እንደ ሥጋና እንደ ነፍስ የተዋሐዱ ናቸው:: አንዱ ከአንዱ ቢለይ ነፍስ የሌለው ሥጋ እንደማለት ነው:: ጥሩ ምግባር የሚኖረን በሕገ እግዚአብሔር ስንመራ በመሆኑ ሕግጋትን መጠበቅ አንዱ የድኅነት መንገድ ነው:: 1ኛ ዮሐ 2÷29፣ 1ኛ ዮሐ3÷9–10:: እምነት አለኝ እያለ መልካም ምግባር የሌለሙ ዲያብሎስ ብቻ ነው:: መልካም ምግባር የቀና ሃይማኖት መገለጫ ናትና::

## መንፈሳዊ ተጋድሎ

መንፈሳዊ ተግድሎ ሥጋን ለነፍስ ለማስገዛትና በፈቃደ እግዚአብሔር መኖር በመሆኑ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ይገኛል:: አባቶች መነኮሳት እናቶች መነኮሳይያት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ«የዲያቢሎስን ሽንገላ ት ቋሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና» ኤፌ 6÷10–12 እንዳለ ጻዋ ለብሰው ፣ ጤዛ ልሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው ከጽልመት አበጋዝ ከዲያብሎስ ጋር እየታገሉ በገዳም በአት ወስነው መኖራቸው ለመዳን ነው:: ምናልባት ይህን መንፈሳዊ ተጋድሎ ማድረግ የተሳናቸውና በዚህ ሥጋን በሚያደክም ሕይወት ለማለፍ የማይሹ ወገኖች ራሳቸውን በማታለያ መጋረጃ ሸፍነው ድኅነት በጸጋ እንጂ በተጋድሎ አይደለም በማለት በመንፈሳዊ ተጋድሎ ያሉትን የሚነቅፉ አሉ:: ነገር ግን እውነታው ከላይ የተባለው ነው:: ወደ ሕይወት የሚወስደውን መንገድ ጠባብ የሚያደርገውም በክርስትና ሕይወት ውስጥ ጽኑ መንፈሳዊ ተጋድሎ የግድ በማስፈለጉ ነው:: ማቴ 7÷13–14 ለመሆኑ ድኅነት ያገኝ ዘንድ የሰው ልጅ ሥጋውን የሚጐስምባቸውና ለፈቃደ እግዚአብሔር

የሚያስገዛባቸው መንፈሳዊ ተጋድሎዎች የትኞቹ ናቸው? ቀጥለን ጥቂቶቹን እናያለን፡፡

## ሀ. ጾም

ጾም የሥጋን ምኞት የምታጠፋ የነፍስን ቁስል የምታድርቅ ለጐልማሶችም ጸጥታንና እርጋታን የምታስተምር ስትሆን የጸሎት እናት የእንባ ምንጭ የጽድቅ መሠረትም ትባላለች፡፡ በብሉይ ኪዳን ያለው ጾም ሥጋዊ ችግርን ለማስወገድ የሚጾም ነበር፡፡ በሐዲስ ኪዳን ግን የሚጾመው ለጽድቅ ነው፡፡ «እናንተ አሁን የምትራቡ/የምትጾሙ/ ብፁአን ናችሁ ትጠግባላችሁና» ሉ ቃ 6÷21፡፡

ጾም የጽድቅ መሠረት ነው፡፡ ይህንንም ጌታችን 40 ቀንና 40 ሌሊት በመጾም አሳይቶናል፡፡ ማቴ 4÷4 በተጨማሪም ጾም የክርስቲያኖች መንፈሳዊ ግዴታ መሆኑንና ሲጾሙም በምን ዓይነት መጾም እንደሚገባቸው ሲያስረዳ «ስትጦሙም እንደ ግብዞች አትጠውልጉ» ብሏል፡፡ ማቴ 6÷16 ሐዋርያትም ይጾሙ ነበር፡፡ የሐዋ 13÷3፡፡ ጾምም ሲባል ሥጋን አለምልመው የነፍስን ፈ ቃድ/ ፍቅር፣ ትኅትና ከሚያቀጭጩ መባልዕት ለተወሰኑ ጊዜያት መከልከልና ሕዋሳትን በሕገ እግዚአብሔር መምራት ነው፡፡

## ለ. ጸሎት

ጸሎት ከእግዚአብሔር ከአምላካችን ጋር የምንገናኝበት የምንወያይበት ነው፡፡ ክርስቲያን ከሚመጣው አደጋ ሁሉ በጸሎት ይድናል፡፡ ለሰማያዊውም ክብር ይበ ቃል፡፡ ጌታ በመዋዕለ ሥጋዌው ለእኛ አብነት ሊሆነን ይጸልይ ነበር፡፡ ማቴ 26÷39–42፡፡ ለሐዋርያቱም «ወደፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ» ብሏቸዋል፡፡ ሉ ቃ 22÷40፡፡

## ሐ. ስግደት

ከመንፈሳዊ ተግባራት አንዱ ስግደት ነው፡፡ በስግደት ሥጋችንን እንጐስግለን፡፡ ለእግዚአብሔር መገዛታችንን እንገልጻለን፡፡ ጉልበት ሁሉ ለጌታችን መንበርከክ እንደሚገባውም በወንጌል ተጽፏል፡፡ ፊል 2÷10

በአጠቃላይ ሐዋርያት «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል» እንዳሉ የሐዋ 14÷22 የሰው ልጅ ይድን ዘንድ ከእርሱ የሚጠበቁትን ማድረግ ይጠበቅበታል።

እንግዲህ ፈጣሪ ዓለማት እግዚአብሐር በዲያብሎስ ምክር የምትመጣ የሲያልን መንገድ ትተን በእርሱ ምክር የምትገኝ በገነት መንገድ ብንጓዝ እንደምንጠቀም አስተምሮ የፈለግነውን ለመምረጥ አልከለከለንም ማለት ነው። ነገር ግን እዚህ ላይ አንዳንድ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ነገሮችን በመጥቀስና ልባቸው ያቀበላቸውን በመናገር የሰው ልጅ በድኅነቱ ውስጥ ምንም ዓይነት ድርሻ አይጠበቅበትም የሚል ሀሳብ ያቀርባሉ። ነገር ግን ይህ ሀሳባቸው የተሳሳተ ነው። እስቲ እንደምሳሌ ጥቂቶቹን እንመልከት።

በመጀመሪያ የምናየው በጸጋው ድነናል የሚሉትን ክፍሎች ነው።

<u>እነዚህ ክፍሎች</u> ፣

ሕገ እግዚአብሔርን አምዘግዝገው ጥለው «ድኅነት የሚገኘው በጸጋ ብቻ ነው» ይላሉ። ይህ ግን የእግዚአብሔርን ቃልና ትዕዛዝ የሚቃወም የሐሰት ትምህርት ነው።

አምላክ ሰውን ያዳነው የሰው ልጅ ሕግጋትን /ትዕዛዘ እግዚአብሔርን ፈጽሞ በመገኘቱ ሳይሆን እንዲሁ በርኅራኄው፣ በቸርነቱ፣ በጸጋው ሊያድነው በመፈለጉ ነው። ሰው በተሰጠው ነጻ ፈቃድ ተጠቅሞ አትብላ የተባለውን በልቶ ጸጋውንና ክብሩን ቢያጣ፣ ተሰጥቶት የነበረውም ሙሉ ነጻ ፈቃድ ጐደሎ ቢሆንበት በበደሉ ተጸጽቶ ንስሐ ቢገባ እግዚአብሔር የቀድሞውን ሙሉ ነጻነቱን ሊመልስለት ተስፋ ሰጠው። ሕይወትንና ሞትንም በፊቱ አኑሮ የፈቀደውን እንዲመርጥ ሥልጣንን ሊሰጠው ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ አዳነው።

በዚህ ማዳኑ ውስጥ ታዲያ የድኅነቱ ተጠቃሚ የሆነው የሰው ልጅ ይድን ዘንድ ማድረግ የሚገባውን ሁሉ በማድረግ አሳይቶታል።

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ማለትም በሥላሴ አንድነትና ሦስትነት በማመን በፍቅሩ እንዲኖር በባሕርይ ልጁ አስተምሮታል። ዮሐ 3÷31-36። ዮሐ 5÷24። የሕይወትን መንገድ ከፍቶ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» ብሎ ቢበድል ከበደሉ

የሚነጻበትን የንስሐ በር ከፍቶለታል፡፡ ማቴ 4÷17፡፡ ኃይልና ብርታትን አግኝቶ ዲያቢሎስን እንዲያሸንፍ ከእርሱ ጋር አንድ ሆኖ ይኖር ዘንድ ሥጋውንና ደሙን ሰጥቶታል፡፡ ዮሐ 6÷53–59፡፡

«እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ አዳነ» ማለት «ዕዳችን ተከፍሏል ድካማችን ተጿል፣ የድኅነት መንገዱ ተከፍቷል» ማለት ነው፡፡ በዚህ ነገር «እሺ» ብሎ ለመጠቀም «እምቢ» ብሎ ለመጐዳት ለሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ወደ በጐ ነገር /ወደ ድኅነት/ ይመልሰዋል እንጂ በግድ ጐትቶ አያመጣም፡፡ ይህም «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» ባለው ይታወቋል፡፡ ዮሐ 14÷15፡፡ ማንም የወደደ ትእዛዙን ጠብቆ የመጠቀም፣ ያልወደደም ባለመጠበቅ ሊጐዳ ነጻ ፈቋድ አለው፡፡ ጌታችን አልዓዛርን ከመቃብር ሲያስነሣ የመቃብሩን ድንጋይ ሰዎች እንዲያነሡ ሲያደርግ እርሱ ግን ሙቱን ጠርቶ አስነሣ፡፡ ይህንን ማድረጉ ሰው በድኅነቱ ላይ የራሱ የሆነ ድርሻ እንዳለው ለማሳየት ነው፡፡

ይህች መጽሐፍ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ትሰጣለች፡፡

- ለአዳም መሳሳት ተጠያቂው ማነው?
- የአዳም ውድቀት ስንል ምን ማለታችን ነው?
- ለአዳም የሚያስፈልገው ማነው?
- እግዚአብሔር ለምን ሰው ሆነ?
- እግዚአብሔር ሰውን እንዴት አዳነው?
- እግዚአብሔር ሰው ሆነ ስንል እንዴት ነው?
- በነገረ ድኅነት ውስጥ የሰው ልጅ ድርሻ ምንድን ነው?

በተጨማሪ በነገረ ድኅነት ውስጥ የድንግል ማርያም ድርሻ ምን እንደሆነ ታስረዳለች፡፡

አዘጋጅ፡- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል
1993 ዓ.ም.

ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ